# መርህ - ፖሊሲ

BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

ተዛማጅ ግብአቶች:- CNA-RA, ECC-RA, EGI-RA, IAA, IGT-RA, IQB-RA, IQD-RA, JEA-RA, JEC-RA, JFA-RA, JGA-RA, JGB-RA, JOA-RA, KEA-RA
ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት:- Deputy Superintendent of Teaching, Learning, and Programs
ተዛማጅ ምንጭ:- COMAR 13A.08.01.03; Annotated Code of Maryland, Education §7-308

## የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች

A. ዓላማ

ተማሪዎች በትምህርት ሒደት ተሰማርተው እያለ በመካከላቸው አእምሯዊ ብስለትን፣ ዜግነትን፣ የሃላፊነት ስሜትን፣ እና የመከባበር ስሜትን በሚማረው ህብረሰብ መካከል ለማዳበርና ለማሳደግ የተነደፈ ነው። የዚህ ማህበረሰብ አባላት እንደመሆናቸው መጠን፣ ሁሉም ተማሪዎች እርግጠኛ መብቶች፣ ኃላፊነቶች፣ እና የተለዩ ጥቅሞች/ክብሮች አሏቸው። ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና ለተማሪዎቹ ትምህርታዊ ግቦች የሚተገበሩበት አመቺነት ያለው አካባቢ በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ የሚጠበቁ ስነምግባሮች አሉ።

B. ጉዳዩ

ነፃ እና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ማህበረሰብ መብቶች ከኃላፊነት-ተጠያቂነት ጋር ተመጣጣኝነት/ተጓዳኝነት አለው። መብቶች በጠቅላላ በተፈጥሮ ከኃላፊነት-ተጠያቂነት ጋር አብረው የተጋመዱ/የተቆራኙ ናቸው።

C. አቋም

1. ተማሪዎች ስለራሳቸው ትምህርት፣ ስለ ግል ባህሪያቸው፣ እና መብቶቻቸውን ስለሚጠቀሙበት ስነምግባር ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በትምህርት ማህበረሰብ በንቃት እንዲሳተፉ፣ በድርጊታቸው ምክንያት የሚያስከትለውን ተጠያቂነት እንዲቀበሉ፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መርሆችን እና ደምቦችን እንዲያከብሩ ይጠበቃል።

2. የተማሪዎች መብት ሁልጊዜም ሌሎች ሰዎች፣ ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችን፣ ወላጆችን፣ እና ማህበረሰቡን ጨምሮ ካላቸው ህጋዊ መብቶች እና ኃላፊነቶች አንፃር መታየት ይኖርበታል።

3. በትምህርት ማህበረሰብ ንቁ ተሳትፎ አካል እንደመሆኑ መጠን፣ የስቴት እና የአካባቢ ህጎች፣ መርሆች፣ ደምቦች፣ እና የአሠራር ሒደቶች በሚፈቅዱት መሠረት ተማሪዎች ክለቦችን፣ ቡድኖችን፣ እና የተማሪ ድርጅቶችን በመመስረት ተሳትፎ ማድረግ ይችላሉ።

4. የተማሪ አመራር በመሆን ወይም ለሌላ የአመራር ኃላፊነት ቦታዎች የተመረጡ ተማሪዎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ትምህርታዊ ብቁነታቸው መጠበቅ ይኖርበታል።

5. ለተመራጭነት ወይም በተማሪ አመራርነት የሃላፊነት ቦታዎችን ለመያዝ ለመመረጥ የሚሹ ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት ካምፓስ ዉስጥ እና ዉጪ ስነምግባራዊ፣ ህጋዊ እና ተገቢነት ያለው ባህርይ ምሳሌነት ያለው

ስነምግባር ማሳየት እና ሁሉንም መርሆች፣ ደንቦች፣ እና አሰራሮችን/ስነስርአቶችን መተግበርና ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ከተማሪዎች ጋር እና/ወይም ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ ስለ ብቃታቸው የመወሰን ኃላፊነት የርእሰመምህሩ(ሯ) ነው።

6. በአለባበስ ባህርይ፣ በስነጽሑፍ፣ እና ሌሎች የመገለጫ መብቶች አመቺ የትምህርት ድባብ/ምህዳርን ከመጠበቅ አኳያ ተስማሚ መሆኑን የመጠበቅ ሃላፊነት ጋር የተገናዘበ/ተመዛዛኝነት ያለው መሆን አለበት።

7. የሃይማኖት ነፃነት መብቶች በህጉ መሠረት መከበር እና መስተናገድ አለባቸው።

8. ተማሪዎች በትምህርት ቤት፣ ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ እንቅስቃሴዎች-አክቲቪቲዎች፣ በ MCPS መጓጓዣ ወደ ትምህርት ቤትና ወደ ቤት ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ እንቅስቃሴዎች ጉዞ ላይ፣ ወይም በትምህርት ቤት የሌሎችን ጤንነት እና ደህንነት በስጋት ላይ የሚጥል፣ ወይም በትምህርት ቤት የሥራ ከንውን ወይም ደህንነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር ተግባር በፈጸሙት በግል ሥነ ምግባራቸው ላይ በመመርኮዝ ብቻ በዲሲፕሊን እርምጃ የመዳኘት መብት አላቸው። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የዲስፕሊን እርምጃው ሚዛናዊ እና ተገቢነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት። የሆነ ሆኖ፣ ተማሪዎች የሚፈጽሙት ድርጊት የሚያስከትለውን ተጠያቂነት የመቀበል እና ለመማር ማስተማር አመቺ ሁኔታን ለመጠበቅ ንቁ ተሳታፊዎች የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።

9. በአስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት የአካል ማገቻ መጠቀም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ተማሪዎች በአካላዊ ነፃነት የመሆን-የመንቀሳቀስ መብት አላቸው።

10. ህጋዊ እውቅና ያለው የተማሪ ብትህውነት-privacy መከበር አለበት።

11. የተማሪዎች፣ የመምህራን፣ እና የሠራተኞች በሙሉ አስፈላጊ ክብራቸው እውቅና የሚሰጠው እና ይህንኑ ለመጠበቅ፣ ለማክበር፣ እና ለመማር ማስተማር አመቺ ምህዳርን መደገፍ እና በብዙሃን የማህበረሰብ አባላት እንዲደገፍ የማድረግ ሃላፊነት እንደተጠበቀ ይሆናል።

12. ተማሪዎች መከበር ያለበት የፍትህ ሂደት መብቶች አላቸው።

13. የአካባቢ ትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች፣ ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመተባበር፣ በኤክስትራካሪኩለር ወይም ሌላ ከትምህርት ቤት ጋር የሚገናኙ እንቅስቃሴዎች ወይም ሁነቶች ላይ ስለመሣተፍ የዲስፕሊን መርኅ ማዘጋጀት፣ ገደብ ማብጀት፣ እና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል። የመመረቂያ ሥርአት ከሚከበርበት ማስወገድ በአካባቢ ትምህርት ቤቶች መርኅ አይካተትም፤ ነገር ግን፣ ርእሰመህራን ተማሪዎችን የሚመለከት እያንዳንዱን ጉዳይ በተናጠል አጣርተው የምረቃ ስነሥርአት ከሚከበርበት እንዳይሳተፉ መከልከል ይችላሉ።

14. ተማሪዎች በ MCPS ፖሊሲዎች እና ደምቦች የተገለጹት እና እንዲሁም በህግ የተደነገጉ መብቶች እና ኃላፊነቶች አሏቸው።

D. ተፈላጊ ውጤቶች

MCPS የአምሮ እውቀትን ለማዳበር፣ ኃላፊነት፣ ዜግነት፣ ግላዊ ክብርን ስለማክበር፣ እና ህጋዊ ኃላፊነቶችን ስለማክበር አመቺ የተምህርት ድባብ/ምህዳር ይፈጥራል።

E. የአፈጻጸም መመሪያዎች

1. ስለ መብቶች እና ኃላፊነቶች የተማሪዎች መመሪያ - Student's Guide to Rights and Responsibilities በሁሉም የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሰጠት አለበት እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

ለሚገቡ ተማሪዎች በሙሉ መሠጠት አለበት። የዶኩመንት ቅጅዎች ለወላጆች መሰጠት አለባቸው።

2 የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ስለማድረግ እና ስለኤክስትራከሪኩለር እንቅስቃሴዎችን ጉዳዮችን በሚመለከት ከተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ከወላጆች አስተዋጽኦ-ግብአት በማሰባሰብ የአፈጻጸም ደምቦችን-መመሪያዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

**F. ግምገማ እና ዘገባ**

ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ነው።

**የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፦** Adopted by Resolution No.19-97, January 14, 1997; Amended by Resolution No. 197-04, March 22, 2004; amended by Resolution No. 193-07, April 19, 2007, amended by Resolution No. 316-14, June 30, 2014.

**ስለዚህ ፖሊሲ የቀድሞ ታሪክ፦**ይህ ፖሊሲ ቀደም ሲል በተማሪ መብቶች እና ግዴታዎች መምሪያ መጽሐፍ Section M ላይ የተካተተ ነበር ።